# ግንቦት ሰባትን፣ ወሐቢያንና ስደተኛውን ሲኖዶስ ምን አገናኛቸው?

ዘሩባቤል ማቲያስ - 6/8/12

*ከሳምንታት በፊት እንዲህ ሆነላችሁ፡፡ …*

ደባው የተቀመረው አሜሪካ ውስጥ ነው። ተቀምሮም አልቀረም–አስመራ ውስጥ ባሉት የትርምስ ባለሟሎች እንዲጎለብትም ተልኳል። ተልኮም አልቀረም–እንደገና በንጹሐን ደም ለመነገድ ወደሚፈልጉት የያኔዎቹ የቅንጅት ነውጠኛ አመራሮች ወዳሉበት ዋሽንግተን ተመለሰ፡፡ ዓላማው በባዶ ሜዳ ላይ የሰላማዊ ዜጎችን የመብት ጥያቄ የራስ አድርጎ የጥፋት እምቢልታ በመንፋት ሁሉንም ወገኖች የማስተባበር ጥረት ነው፡፡

የእምቢልታውን እጀታ የያዙት "ዶክተር ኢኮኖሚስት" እና እንደ በቀቀን እርሳቸው ያሉትን ሳይቀንስና ሳይጨምር የሚለፍፈው "ጣቢያቸው" ናቸው። ሽብርተኝነትን ከጡት አባታቸው ሻዕቢያ ልቅም አድርገው ለተማሩት ለእነዚህ አስለፍፊና ለፋፊ ማንኛውም ተግባር የስልጣን መወጣጫ መሰላል ሆኖ ነው የሚታያቸው፡፡

ሁሌም ቢሆን፣ በውናቸውም ይሁን በህልማቸው የሚታያቸው ሀገራችን ውስጥ በሚነሳ ነውጥ ሳቢያ የብሔሮችን፣ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን መብት ደፍቀው ዙፋን ላይ ሲወጡ ነው። እርግጥ ይህ ህልማቸው "ድሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ፤ ንጣት ይገድለው ነበር" የሚለው ሀገርኛ ብሂል የሚያስታውሰን ቢሆንም፤ ትናንትም ይሁን ዛሬ የሽብር አርበኞቹ ግን የስልጣን ምት መትቷቸው "ንጣት በንጣት" ሆነው እንሆ ከአንድ አጀንዳ ወደሌላው እየዘለሉ ንጣታቸውን በአሜሪካዊ አይስክሬም ሊያወዙት እየሞከሩ ነው፡፡

ወዛቸው ግን የምፅዓት ቀን ካልመጣ በስተቀር ከቶም ብቅ የሚል አይመስልም፡፡ በየጊዜው በሚደርስባቸው የአጀንዳ ሽንፈት ምክንያት፤ ሥረ-ነገሩን በማጣመም ለፍፈው ያስለፈፏቸው የዜጎች ሰላማዊ ጥያቄዎች ምላሽ በማይገኝበት ባዶ አየር (vaccum) ውስጥ የተናገሩ ይመስል ሰሚ ባለማግኘታቸው አመዳቸው ቡን ብሏል፡፡ ምክንያቱም ጊዜውን ለወሬ ሳይሆን በተግባር ተፈትሾ ውጤት ላመጣለት የዕድገት ሥራ የሰጠው የሀገራችን ህዝብ፤ ባህር ማዶ ቁጭ ብሎ በቆርጦ ቀጥል ዲስኩር የሚያላዝንን "ፌደላዊ" ሳይሆን በተጨባጭ እሱነቱን በመለወጥ ላይ የሚገኘውን ልማታዊውን መንግስት የሚያዳምጥ ከመሆኑም በላይ፣ ለ"እንካ ሰላንቲያ" የሚያውሰው ጆሮ ስለሌለው ነው፡፡

መቼም ውድ አንባቢዎቼ ስለእነማን እያወጋሁ እንደሆነ መገመታችሁ የሚቀር አይመስለኝም፡፡ አዎ! የወጌ ማጠንጠኛ ራሱን ግንቦት 7 እያለ የሚጠራው የሽብር ቡድንን የሚመሩት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ እና የበሬ ወለደ ፕሮፖጋንዳ ማሽናቸው የሆነው " ኢሳት" (አንዳንዶች እሳት ይሉታል) ስለተሰኘው ጣቢያቸው ናቸው። ምንም እንኳን በዛሬው ጽሑፌ አባላቱ እርስ በርስ እየተባሉ ስላሉት የሽብር ቡድኑ እና አፈ-

ቀላጤው ስለሆነው ጣቢያው ማውሳት ባይሆንም፤ የቡድኑንና የሌሎች አክራሪዎችን ጊዜያዊ ጥምረትን በጥቂቱ ለማመላከት እሞክራለሁ።

እርግጥ የሰሞኑ የአጀንዳ ቅብብሎሽ የጥምረት ስበት ማዕከሎቹ ግንቦት 7 እና ኢሳት ናቸው። ታዲያ እዚህ ላይ 'ቢሰምርለት ሀገራችን ውስጥ አመፃን አቀጣጥሎ እሳቱን ባህር ማዶ ቁጭ ብሎ ለመሞቅ የሚመኘው ግንቦት 7፣ የሀገራችንን ህዝበ ሙስሊም ጥያቄዎች የራሱ በማድረግ በሃይማኖት ሽፋን የፖለቲካ ፍላጎቱን ለማሳካት የሚጥረው የጥቂት አክራሪዎች /ወሐቢያ/ ስብስብ እንዲሁም በስደት የሚኖረው ሲኖዶስ (exile synod) ከመሰንበቻው በሙስሊሙ ጥያቄ ላይ ምን አዳበላቸው?' የሚል ጥያቄ በማንሳት የግንኙነታቸውን ሰንሰለት ለመገንዘብ ጠቃሚ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

ሰሞኑን የሙስሊሙን ማህብረሰብ ፍትሐዊና ትክክለኛ የመብት ጥያቄዎችን መንግሥት ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ተከትሎ ምላሽ ለመስጠት በሚንቀሳቀሱበት ወቅት፤ በሀገር ውስጥ ሃይማኖትን ከለላ በማድረግ የሚንቀሳቀሱ ጥቂት አክራሪዎች፣ግንቦት 7፣ ኢሳትና በስደት የሚገኘው ሲኖዶስ የጥፋት ግንባር መፍጠራቸው በእጅጉ የሚያስገርም ነው፡፡ ለአንባቢዎቼ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ እነዚህ በአካል የተለያዩ፣ ነገር ግን በቅኝት የተዋሃዱ የጥፋት ኃይሎች ያስደመጡንን ቅንጅታዊ የአመፅ  ዲስኩር እነሆ ልበል፡-

"ከሙስሊሙ ማህብረሰብ ጎን እንቆማለን!" *-ግንቦት 7 የሽብር ቡድን*

"ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የሚያሳዩት ፍጹም ሰላማዊ የሆነ ተቃውሞ ብዙዎችን እያስደመመ ነው" *-ኢሳት*

"ህዝበ ክርስቲያኑ ከሙስሊሞች ጋር በተቃውሞ ይተባበር!" *-በስደት የሚገኘው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን*

እርግጥ ከትክክለኛው ምግባራዊ ምልከታ አኳያ ብንነሳ ሽብርን የሚያራምደው ቡድንና አፈ - ቀላጤው፣ ሃይማኖትን ተገን አድርጎ የፖለቲካ አጀንዳን ለማራመድ የሚሻ አክራሪን እንዲሁም በክርስትና እምነት የተቋቋመው ስደተኛው ሲኖዶስ የሚያገናኛቸው ተጨባጭ ምድራዊም ይሁን ሰማያዊ  አግባብ አለ ብሎ ለመናገር አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም የሽብር ቡድኑ ዕድሉ ካጋጠመው በግብረ - ሽበራ ተግባሩ ሙስሊሙንም ሆነ ክርስቲያኑን ከመፍጀት ወደ ኋላ የሚል ባለመሆኑ ነው፡፡

'ኢሳት'  የተሰኘው የውሸት ማቀነባበሪያ ፋብሪካውም ቢሆን፤ ዘር ከዘር እየለየ 'ያዘው፣ በለው'ይል የነበረውና ከ800 ሺህ በላይ ንፁሃን ሰዎች ለህልፈተ ህይወት እንዲዳረጉ እንዳደረገው የሩዋንዳው 'ሬዲዮ ፍራንስ ኮሊንስ' ዓይነት ተግባርን በገራችን ላይ ገቢራዊ ለማድረግ ያቆበቆበ ጣቢያ ነበር – ነገሩ "ነበር፣ ባይሰበር" እንዲሉት ዓይነት ሆነበት እንጂ፡፡ ታዲያ ከዚህ እውነታ የምንገነዘበው ሃቅ ቢኖር፤  ግንቦት ሰባትም ሆነ በአምሳያው  ጠፍጥፎ  የሰራው 'ኢሳት' ዘር፣ ቀለምና ሃይማኖት ሳይለዩ በሁሉም ኢትዮጵያዊያን ላይ በሴራ ለመዝመት የሚሹ መሆናቸውን  ነው፡፡

ሆኖም እዚህ ላይ ውድ አንባቢያን 'እነዚህ ኃይሎች እንዴት ሊገናኙ ቻሉ?' የሚል ጥያቄ  ልታነሱ እንደምትችሉ እገምታለሁ፡፡ እርግጥም ጥያቄው ተገቢ ሲሆን፤ ምላሹም እንዲህ የሚነበብ ነው፡፡ …እንደሚታወቀው ሀገራችንን በመምራት ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ  መንግስት ሀገሪቱን በሽብርና በአመፅ

ለማተራመስ የሚደረጉ ማናቸውንም ተግባራት የመከላከልና የመቆጣጠር ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ፣ በሰላማዊ የፖለቲካ ምህዳር ተወዳድረው በህዝብ የተተፉ እንደ ግንቦት ሰባት ዓይነት ቡድኖች ሀገራችን ምን ጊዜም ሰላማዊ ሆና ዕድገቷን ለማየት የሚፈልጉ አይደሉም፡፡ በመሆኑም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኢትዮጵያን ለማተራመስ በአመለካከት እሳትና ጭድ የሆኑ ኃይሎችን እንኳን ሳይቀር የአጀንዳቸው ማስፈጸሚያ ሊያደርጓቸው ይፈልጋሉ፡፡

አሸባሪው ግንቦት ሰባት "ከሙስሊሙ ማህረሰብ ጎን እንቆማለን" ሲል 'አጀንዳህ አጀንዳዬ በመሆኑ ማናቸውንም ድጋፍ አደርግልሃለሁ' እያለ ለመሆኑ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን ሀገራችን ውስጥ ህዝበ - ሙስሊሙን የማይወክሉ ጥቂት "የሃይማኖት ነጋዴዎች" በአክራሪነት ተሰልፈው የአብዛኛውን የእምነቱን ተከታይ አግባብ ያለውን ጥያቄ ገልብጠው አጡዘውታል። ይህም በአሸባሪው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የሚመራው ቡድን ጥቂት አክራሪዎችን ብዛት እንዳለው ህዝብ በመቁጠር ሁኔታውን ከተፈጥሮአዊ ባህሪው ውጭ ለማሳየት የተጠቀመበት ስልት የነውጥ አቀጣጣይነት ፍላጎቱን በገሃድ የሚያስረዳ ነው፡፡

እርግጥ የአሸባሪው ቡድን አጀንዳ አስፈጻሚ ፍለጋ ሩጫ፣ በጣቢያው ጭምር የታገዘ ነው፡፡ በሀገር ውስጥ ያለው አክራሪ ኃይልን የራሱ አጋር አድርጎ ለመቁጠር የግብረ - ሸበራ ማራመጃ ጣቢያውን በቀስቃሽነት ይጠቀማል፡፡ ለዚህም ነው ህዝቦችን የሚያጫርስ እሳት የሚለኩሰው 'ኢሳት' የተሰኘ የበሬ ወለደ ቀማሪ ጣቢያ፣ የጉዳዩ ባለቤት የሆነውን አብዛኛውን የሙስሊም ማህበረሰብ 'ሰላማዊ የሆነ ተቃውሞው አስደምሞኛል' በማለት ጥሪውን ሊያስተላልፍ የነበረው፡፡ ግና ጥሪው ምን ዋጋ አለው?– እንደ ሐምሌ ጸሐይ እንደናፈቀው ቀርቷል፡፡

ምንም እንኳን በአንድ ሀገር ውስጥ ልማትና ዴሞክራሲ የግድ መሳ ለመሳ ይሄዳሉ ባይባልም፣ ሀገራችን ግን በዓለም አቀፉ ማህብረሰብ "እንቱታን" ያተረፈላትን የልማት ዕድገት በማሳካት ላይ የምትገኝ ሲሆን፣ በዴሞክራሲውም ረገድ ከራሷ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ ሂደቱን እየገነባች ነው–ዴሞክራሲ እንደ ቁሳቁስ ከውጭ የሚገባ አይደለምና። ህዝቡን በግብረ - ሽበራ ተግባር ለመጨፍለቅ የተነሱት ግንቦት ሰባት እና እነ አበበ ገላው በሚያስገርም ሁኔታ በጋዜጠኝነት ሽፋን በአደባባይ ስለ "ነጻነት" ለመለፈፍ ቢሞክሩም፣ መንግስት እና ህዝብ መቼም ቢሆን የሀገራችንን ዕድገትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታችንን የኋሊት ሊቀለብሱ የሚሹ ሴረኞችን ሊያስተናግዱ የሚችሉበት ምህዳር እንዲሁም ተግባራቸውን ከቁብ እንደማይቆጥሩት ሊረዱት ይገባል።

እነ አሸባሪው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ከፖለቲካ ጋር ምንም ዓይነት ቁርኝት ሊኖራቸው የማይገባቸውን የሃይማኖት አባቶች መጠቀሚያ ማድረግ የጀመሩት ዛሬ አይደለም፡፡ የዛሬ ሰባት ዓመት ገደማ በተካሄደው ሦስተኛው የሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ወቅት፣ ግለሰቡ ህገ - መንግስታዊ ስርዓቱን በኀዳና ላይ አመጽ ለመናድ የነውጠኛው ቅንጅት አመራር አባል ሆነው አሜሪካ በስደት የሚገኙትን የኦርቶዶክስ ሲኖዶስ አባቶችን በአደባባይ አሰልፈው ተቃውሞ እንዲያሰሙ አድርገዋል፡፡

ምንም እንኳን የሰሞኑ አጀንዳ ምርጫ ባይሆንም፤ እነዚህ አባቶች በሃይማኖት ሽፋን የሚንቀሳቀሱ ጥቂት የሙስሊም አክራሪዎችን እንዲደግፉ በእምነት የማይገናኟቸው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መግለጫ እንዲያውጡ በማድረግ ተጠቅመውባቸዋል፡፡ ለዚህም ነው ባለፈው ሰሞን በአቡነ መልከ ፀዴቅ የሚመራውና በስደት የሚገኘው የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ "ህዝበ ክርስቲያኑ ከሙስሊሞች ጋር በተቃውሞ ይተባበር!" በማለት መግለጫ ያወጣው።

ይህ መግለጫ በ'ኢሳት' ጣቢያ መነገሩ ደግሞ የትስስሩን ቁርኝት ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በሻገርም፤ የሽብር ቡድኑና አፈ - ቀላጤው የከሰረ የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማሳካት በ"ላም አለኝ በሰማይ፣ ወተቷንም አላይ" የቅዥት ዓለም ምኞት የማይቧጥጡት የጥፋት አቀበት እንዲሁም የማይንደረደሩት የሽፋጥ ቁልቁለት የሌለ መሆኑን በህያው አስረጅነት የሚያስገነዝበን ነው፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ግንቦት ሰባት የተሰኘው የሽብር ቡድንን፣ ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገው ጥቂት የሀገር ውስጥ አክራሪ ቡድንን እና በስደት ውጭ የሚገኘውን የኦርቶዶክስ ሲኖዶስን ከቆሙለት ግብ አኳያ በቀጥታ የሚያገናኛቸው ነገር ባይኖርም፤ መግለጫቸው በመንፈስ አንድ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ ምክንያቱም ሦስቱም አካላት በፀረ - ህገ - መንግስታዊነት የተሰለፉ በመሆናቸው ነው፡፡

የሽብር ቡድኑ ምድራዊ ስልጣንና ከህገ - መንግስታዊ ሥርዓቱ አግባብ ውጭ በአመጽ ለመቆናጠጥ የሚሻ የቀቢጸ - ተስፈኞች ስብስብ ሲሆን፤ ሃይማኖታዊ ንግድ የሚያካሂዱት ጥቂት የሙስሊም አክራሪዎች ደግሞ የህዝቦችን የሃይማኖት እኩልነትንና የእምነት ነጻነትን በመጻረር ህገ - መንግስቱን ለመናድ የተሰለፉ ሃይማኖተኛ ያልሆኑ ፖለቲከኞች ናቸው፡፡ ለተከታዩቻቸው "ሰማያዊ" ጽድቅን ለማስገኘት መስራት የሚገባቸው የስደተኛው ኦርቶዶክስ እምነት አባቶችም ቢሆኑ፤ በይፋ ፖለቲካ ውስጥ በመግባት ፀረ - ህገ - መንግስታዊ ኃይሎችን ደግፈው ከመቆማቸውም በላይ፤ መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩበትን ድንበር ለማፍረስ መጣራቸውን እንገነዘባለን፡፡

እንደሚታወቀው ማንኛውም ሃይማኖት ሰላምን እንጂ አመጽን አይሰብክም፡፡ ስለሰማያዊ ጽድቅ እንጂ፤ ፖለቲካ ውስጥ በገሃድ ገብቶ የምድራዊ ስልጣን አላሚዎችን አይደግፍም፡፡ በሃይማኖትና በመንግስት መካከል ያለውን ግንኙነትም ያከብራል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ "የቄሳርን ለቄሳር፣ የኢየሱስን ለኢየሱስ" ተብሎ የተጻፈውን ቅዱስ ቃል ለምዕመናኑ ያስተምራል እንጂ፤ መንግስትና ሃይማኖት የሚለያዩበትን ገመድ በጥሶ የፖለቲካ ሰባኪ መሆን አይጠበቅበትም፡፡ ይሁንና በስደት የሚገኘው የኦርቶዶክስ ሲኖዶስ፤ ቅዱስ ቃሉን ተከትሎ አባታዊ ሚናውን መወጣት ሲገባው፣ ከዚህ በተጻራሪ ቆሞ "ፖለቲካዊ ሃይማኖት አራማጅ" መሆኑ በማንኛውም መስፈርት ተቀባይነት ያለው አይመስለኝም፡፡ ለምን ቢባል፤ ተግባሩ 'ለምዕመናን ሰላምንና መቻቻልን ስበክ' ከሚለው ከራሱ ቀኖና ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን ሦስቱንም አካላት የሚያገናኛቸው ጉዳይ፤ የሀገራችን መንግስትና ህዝብ ኢትዮጵያን ለማተራመስ የሚደረጉ ስራዎችን ለመቆጣጠር ፀረ - ህገ - መንግስታዊ ኃይሎችን የማጥራት ስራ ሲያከናውኑ በየፊናቸው 'ወላፈኑ እኛንና የሀገር ውስጥ ተላላኪዎቻችንን ሊነካ ይችላል' ብለው ስለሚሰጉ ነው፡፡ ዳሩ ግን በግንቦት ሰባት እና በኢሳት አጀንዳ ፈጣሪነት የሚወጡ ማናቸውም "አመጽን

እንደግፋለን” የሚሉ ጥሪዎችም ይሁኑ መግለጫዎች  መንግስት እና ህዝብ የሚያከናውኑትን ፀረ - ህገ - መንግስታዊ ኃይሎችን የማጋለጥና ሴራቸው እርቃኑን እንዲወጣ የማድረግ ቁርጠኛ አቋማቸውን ከቶም ሊገታው የሚችል አይደለም፡፡ በአካል ተለያይተው በመንፈስ አንደ የሆኑት የህገ - መንግስቱ ቀበኛ ኃይሎች እንዲያው “አልን” ለማለት ካልፈለጉ በስተቀር፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት እንደ ትናንቱ ሁሉ፣ ዛሬም ሆነ ነገ ፀረ - ህገ - መንግስታዊ ኃይሎችን የሚሸከሙበት ትከሻ አይኖራቸውም፡፡ ሰላም ወዳዱ የሀገራችን  ህዝብ ራሱንና  ሀገሩን ከአስከፊው ድህነት ለማላቀቅ ቀን ከለሊት ሙሉ ኃይሉን  ስራ ላይ አውሏል፡፡ መንግስትም ካለፉት ሥርዓቶች ሲንከባለሉ የመጡትን የሠላም የልማትና የዴሞክራሲ ችግሮችን  በየደረጃው  ለመፍታት ርብርብ እያደረገ ነው፡፡ የሀገሪቱን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና  ህዝቦችን የሌሎች ሀገሮች የደረሱበት የዕድገት  መሰላል ላይ ለማውጣት ያደረጋቸው ጥረቶች ፍሬ  አፍርተው  አብነታዊ ተጠቃሽ እንድንሆን  በማድረግ  ላይ ይገኛል፡፡ እናም የፍሬው ተጠቃሚ የሆነው ህዝብም ይሁን ሀገሪቱን ካለችበት የድህነት አረንቋ ለማውጣት ባተሌ የሆነው መንግስት የአመጽ አታም ደላቂዎችን ማየትም ሆነ መስማት አይሹም፡፡

ይህ እምነታቸውም በሰሞኑ “የአንድ ሳንቲም ሦስት ገጽታ” ሆነው ጥቂት የእስልምና ሃይማኖትን በግርዶሽነት የሚጠቀሙ አክራሪዎችን “እንደግፋለን” በማለት ያጯጯኹትን  የአመጽ ጥሪ “ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ” በሚል ምልከታ አክሽፈውታል፡፡ ጥቂት አክራሪዎች አብዛኛውንና ሠላማዊ ጥያቄ ያለውን ሙስሊሙን ማህበረሰብ የማይወክሉ በመሆናቸው፤ለአብዛኛው ምዕመን በቂ ምላሽ በመስጠት ግንቦት ሰባትና ኢሳት ሲያጫጩሁላቸው የነበሩት ጥቂት በሃይማኖት ሽፋን የሚተራመሱ ግለሰቦች ሴራቸው  በአደባባይ እንዲጋለጥ አድርገዋል፡፡

ይህም በሃይማኖት ሰበብ ሀገራችን ውስጥ ብጥብጥ የሚነሳ የመሰላቸው  አመጽ ናፋቂዎች  የህልም ቅዥታቸው ባዶ ተስፋ መሆኑም በይፋ እንዲታወቅ አደረገ፡፡ ወገግ ባለ ብርሃን ውስጥ እየኖሩ ሁሌም ድቅድቅ ጨለማ የሚታያቸው የዲያስፖራ ጽንፈኛ ፖለቲከኞችም፤ መንግስት ትክክለኛውን የሙስሊሙን ማህብረሰብ ጥያቄ ሲመልስ በራሳቸው  ጽልመት ውስጥ  ተዋጡ፡፡ ኢትዮጵያና  ህዝቦቿ  የቁልቁለት እንድርድሪታቸውን አቋርጠው  አቀበት መውጣት የጀመሩበትን 21ኛ  ዓመት ችቦን  ለኮሱ – በጥቂት ዓመታት ውስጥ  ኢንዱስትሪውን ከፊት ግብርናውን  ከኋላ ሊያደርጉት  ለራሳቸው ቃል እየገቡ፡፡ … ግና ዳግም “የዶክተሩ  ኢኮኖሚስት”  እና የጣቢያቸው ሐሞት  ፈሰሰ፡፡ በሌሎች አጀንዳ ተንጠልጥለው እንደ ነጋዴ ቀብድ ያስያዙት የአመጽ ቧልትም እንዳይሆን ሆኖ ለአስራ ምናምንኛ  ጊዜያት የሽንፈትን ፅዋ እንዲጋቱ ሆነ፡፡…

… በእነዚህ የሽንፈት  ክራሞቶች ጨለማቸው በብርሃን ድል በመነሳቱ ከነጣቢያቸው ማቅ መሰሉ፣ ማቅ ለበሱ፡፡  ወዛቸውም ጠፋ፡፡  ህልማቸውም መከነ፡፡ በአዲስ ቅኝት፣ አስተሳሰብና ዝማሬ የፈካችሁ ሀገራችንና ህዝቦቿ ግን ካለፈው ዓመት የተሻለ ከፍታ ያለውን አቀበት በመውጣት ጉዟቸውን ወደፊት ተያይዘውታል፡፡… ጨለማን ጨለምተኞቹን ወደ ኋላ ዞር ብሎ ላለማየት፡፡…

*እናም ከሣምንታት በኋላም የአመጽ ጥምረቱ  ኪሳራ እንዲህ ተወራረዳላችሁ፡፡…*